# ክላሚድያ ፤ የታካሚ መረጃ

## ይህ መረጃ ለምን ደረሰኝ?

ይህ መረጃ እርስዎ ጋር የደረሰበት ምክንያት፥ ክላሚድያ የሚባለው በሽታ ስላለብዎት ወይም ይኖርብዎታል ተብለው ስለተጠረጠሩ ነው። እዚህ ጽሑፍ ውስጥ ክላሚድያ ስለሚባለው በሽታ እንዲሁም በሽታው ከያዝዎት በኋላ እንዴት እንደሚታከሙ እና እርስዎም ምን ማድረግ እንዳለብዎት መረጃ ያገኛሉ።

## ክላሚድያ ምንድን ነው?

ክላሚድያ በአንድ የባክቴርያ ዓይነት የሚፈጠር በሰፊው የተለመደ በሽታ ነው። በበሽታው ከተለከፉ በሽንት ቧምቧ፣ በሴት ብልት መግቢያ ወይም በፊንጢጣ ውስጥ ክላሚድያ ይገኛል። አልፎ አልፎ ክላሚድያ በግሮሮ ውስጥም ሊገኝ ይችላል።

### ክላሚድያ እንደያዘኝ በምን አውቃለሁ?

በበሽታው የሚለከፉ ብዙ  ሰዎች ምንም ምልክት አያዩም፣ ማለትም በበሽታው መለከፍዎን ሳያውቁ ሊቆዩ ይችላሉ። ሰዎች ለረጅም ግዜ በክላሚድያ ተለክፈው ሊኖሩ ይችላሉ፣ አንዳንዴ ለበርካታ ዓመታት በበሽታው መለከፋቸውን ሳያውቁ ሊኖሩ ይችላል።

አንዳንድ ሰዎች ሽንታቸውን ሲጸዳዱ የሚያቃጥል ህመም ይሰማቸዋል።

በክላሚድያ የተለከፉ ሴቶች ደም የቀላቀለ ፋሳሽ ሊታይባቸው ይችላል፣ ወይም በሆድ እቃቸው የታችኛው ክፍል ላይ ህመም ይሰማቸዋል። ወንዶች ደግሞ ከሽንት ቧንቧቸው የሚወጣ ነጣ ያለ፣ እይታ ወይም ብርሃን የሚያሳልፍ ፈሳሽ ይኖራቸዋል፣ ሌሎች ደግሞ የዘር ፍሬያቸው ውስጥ ህመም ይሰማቸዋል። በፊንጥጣ በኩል የሚስተናገድ ወሲባዊ ግንኙነት የሚፈጽሙት ላይ ከፊንጥጣ የሚወጣ ፈሳሽ ይታይባቸዋል።

### ክላሚድያ አደገኛ ነውን?

በሽታው በሕክምና ካልተወገድ በቀር፣ የሴቶችን የእንቁላል መተላለፊያ አካል ላይ ጉዳት ስለሚያደርስ ጽንስ መያዝን ወይም ማርገዝን አስቸጋሪ ሊያደርግ ይችላል። ጽንሱ ከማህጸን ውጭ እንድያድግ (በኢንግሊዝኛ ectopic pregnancy የሚባለውን) እስከማድረግ ሊያደርስ የሚችል ችግር ሊያስከትልም ይችላል። ወንዶች ላይ የዘር ፍሬያቸው በመበከል ጉዳት ያደርሳል። ክላሚድያ አንዳንድ ግዜ ዐይን ውስጥ ኢንፌክሽን ሊፈጥር ይችላል፣ የአጥንት መገናኛ ላይም ህመም እንዲሰማ ያደርጋል።

## ክላሚዲያ እንዴት ይተላለፋል?

ክላሚዲያ በዋናነት ያለ መከላከያ በሚፈጸም የወሲብ ግንኙነት፤ ማለትም በብልት በኩል በሚደረግ ግንኙነት ወይም በፊንጢጣ በኩል በሚደረግ ግንኙነት ወይም በአፍ በኩል በሚደረግ ግንኙነት ሊተላለፍ ይችላል።  የወሲብ ግንኙነት ከመደረጉ በፊት በሚከናወኑ የገላ መነካካትና በወሲብ ማከናወኛ ቁሳቁሶች አማካይነትም ሊተላለፍ ይችላል። ክላሚድያ ምልክት ሳያሳይም በቀላሉ የመተላለፍ አቅም አለው።

ከክላሚዲያ አይነኬ (immun) መሆን አይቻልም፣ ስለዚህ በሽታው ደጋግሞ ሊይዝዎት ይችላል።

ክላሚድያ በልብስ ወይም በፎጣ ወይም በሽንት ቤት በኩል **አይ**ተላለፍም።

## ክላሚድያን እንዴት ይታከማል፣ ምን ያህል ግዜ ነው በሽታውን እማስተላልፈው?

ክላሚድያን ጸረ ባክቴሪያ ክኒኖች በመውሰድ ይታከሟል። ህክምናው በነጻ ይሰጣል። የታዘዘልዎትን መድሃኒት በሚገባ ከወሰዱና የተነገርዎትን ምክር በውል ከፈጸሙ በሽታው ይወገዳል። ጸረ ባክቴርያ ክኒኖቹን መውሰድ ከጀመሩ ከአሥር ቀናት በኋላ በሽታውን ማስተላለፍ አይችሉም። መድሃኒትዎን በሚገባ ወስደው ካጠናቀቁ በኋላ፣ ከበሽታው ነጻ መሆንዎን ለማወቅ አዲስ ምርመራ ማድረግ አያስፈልጎትም። እርጉዝ ከሆንሽ ግን አዲስ ምርመራ ማድረግ ሊያስፈልግሽ ይችላል።

## በሽታውን |እዳላስተላልፍ ምን ማድረግ አለብኝ?

በተላላፊ በሽታ መከላከያ ደንብ መሰረት፥ ክላሚድያ ለማህበረሰብ አደገኛ በሽታ እንደየሆነ ይቆጠራል። በሽታው ያለብዎት ከሆነ ወይም በሽታው ይኖርብዎታል ተብለው የሚጠረጠሩ ከሆነ፥ መከተል የሚገባዎት ደንቦች አሉ፣ የሥነ-ምግባር ደንቦች ይባላሉ።

### የሥነ-ምግባር ደንቦች

- ወሲብ ለፈጸሙበት ወይም ለፈጸሙበት ሰው፣ ክላሚድያ እንዳለብዎት ወይም ሊኖርብዎት እንደሚችል መንገር ይገባዎታል።
- ህክምናዎን በሚገባ ከማጠናቀቅዎ በፊት ወይም የምርመራዎን ውጤት ከማወቅዎ በፊት፥ ወሲብ የሚፈጽሙ ከሆነ መከላከያ ወይም ኮንዶም መጠቀም ይገባዎታል።
- በህክምና ተቋሙ ወይም በሃኪምዎ ዳግማይ በሚጠሩበት ግዜ መገኘት ይገባዎታል።

በስህተት የተላከ ነው ብለው የሚያስቡት የሥነ-ምግባር ደንቦች መግለጫ ደርሶት ከሆነ፥ በሚኖሩበት አካባቢ ያለውን የተላላፊ በሽታ ሃኪም ጋር መገናኘት ይችላሉ።

ክላሚድያን እየታከሙ ባሉበት ግዜ ውስጥ በሽታው ላይተላለፍ ይችላል በሚል አቦሰጥ ወሲብ አይፈጽሙ። ዋናው አስተማማኙ ነገር፡ የጸረ ባክቴሪያ ክኒን መውሰድ ከጀመሩ አሥር ቀናት ከማለፋቸው በፊት ምንም ዓይነት የወሲብ ግንኙነት አለማድረግ ነው። ያም ሆኖ የግድ ወሲብ መፈጸም ካለብዎት ግን ለወሲብ ግብረ አበርዎ ክላሚድያ እንዳለብዎት መንገርና አንዳች መከላከያ (ኮንዶም) መጠቀም ይገባዎታል።

## የበሽታው መዛመት ክትትል

ክላሚዲያ የያዛቸውን ሰዎች ሁሉ ተከታትሎ ማግኘትና ህክምና እንዲያገኙ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው። አንደኛው ጥቅም፡ በሽታው ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት መቀነስ ሲሆን (ላይ ይመልከቱ)፥ ሌላው ደግሞ ኢንፌክሽኑ ወደ ብዙ ሰዎች እንዳይተላለፍ መግታት ነው።

በተላላፊ በሽታ መከላከያ ደንብ መሰረት፥ በሽታው የተዛመተበትን መስመር በማፈላለግ ሥራ ላይ መተባበር ይገባዎታል። ይህም ማለት፡ ከማን ጋር የወሲብ ግንኙነት ፈጽመው

እንደነበር በሽታ የሚዛመትበትን መስመር ለሚከታተለው ባለ ሙያ መንገር  አለብዎት ማለት ነው። አንዳንድ ግዜ እስከ አንድ ዓመት ያህል ግዜ ወደ ኋላ ሄዶ ማስታወስ ሊጠይቅ ይችላል።

በዚህ አግባብ የሚናገሩት ቃል ሁሉ ለማንም የማይገለጥ በሕግ የተጠበቀ (ሚስጥር) ሲሆን፥ እኒያ እርስዎ የጠቀሷቸው ሰዎች እርስዎ ማን መሆንዎን ሊያውቁ በጭራሽ አይችሉም። እነሱ ምርመራ እንዲያደርጉ ጥሪ ከሚደረግላቸው በቀር ሌላ የሚያውቁት ነገር አይኖርም። እርስዎ የሚሰጡን መረጃ በእርስዎ የህክምና ጁርናል ውስጥ አይሰፍርም። በአንጻሩ የተላላፊ በሽታ መከታተያ መዝገብ (smittspårningshandling) ውስጥ ብቻ ይቀመጣል።

## ተጨማሪ መረጃ

ክላሚድያን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ 1177፣ (በ13 እና 20 ዕድሜ መካከል የምትገኙ ታዳጊዎች) Youmo እና (ታዳጊዎች ማስተናገጃ ድረገጽ) UMO ከታች ባሉት የኢንተርኔት አድራሻዎች ላይ ይገኛል።

www.1177.se www.youmo.se www.umo.se

## ስለ ተላላፊ በሽታ መከላከል በራሪ ወረቀት

የተላላፊ በሽታ በራሪ ወረቀቱ፡ በተላላፊ በሽታ ሃኪሞች ማሕበር የተዘጋጀ እንደመሆኑ መጠን፡ በሃገር አቀፍ ደረጃ ተፈጻሚ ነው።